በጎ ተግባር ማለት መልካም ስነምግባር ነው። ወንጀል ማለት በልብህ ውስጥ የተጣረጠርከውና (የተመላለሰ) ሰዎች ማወቃቸውንም የጠላኸው ነገር ነው።

ከነዋስ ቢን ሰምዓን -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው: ነቢዩ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ ብለዋል፦ «" በጎ ተግባር ማለት መልካም ስነምግባር ነው። ወንጀል ማለት በልብህ ውስጥ የተጣረጠርከውና (የተመላለሰ) ሰዎች ማወቃቸውንም የጠላኸው ነገር ነው።» «ከዋቢሳህ ቢን መዕበድ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: የአላህ መልክተኛ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ዘንድ መጣሁ። እርሳቸውም:
"የመጣኸው ስለበጎ ተግባርና ወንጀል ልትጠይቅ ነውን?" አሉኝ። እኔም: "አዎን" አልኳቸው። እርሳቸውም: "ነፍስህን ፈትሻት! በጎ
ተግባር ነፍስ በርሱ የረጋችበት፣ ቀልብ በርሱ የሰከነችበት ነው። ወንጀል ደግሞ ሰዎችን ፈትዋ ጠይቀህ ፈትዋ ቢሰጡህ እንኳ ነፍስህ ውስጥና ደረትህ ውስጥ የተመላለሰ ነው።" አሉኝ።» [الحديث الأول: رواه مسلم، والحديث الثاني: رواه أحمد والدارمي] [ነው። ሶሒሕ[

ነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ስለበጎ ተግባርና ወንጀል ተናገሩ። እንዲህም አሉ: የበጎ ተግባር ትልቁ ነገር ከአላህ ጋር እርሱን በመፍራት፤ ከፍጡራን ጋር ደግሞ የሚያደርሱብንን አዛ (ችግር) በመቻል፣ ቁጣን በመቀነስ፣ ፊትን በመፍታት፣ ንግግርን በማሳመር፣ ዝምድናን በመቀጠል፣ በመታዘዝ፣ በመራራት፣ በጎ በመስራት፣ መልካም ቤተሰብና ባልደረባ በመሆን መልካም ስነምግባርን መላበስ ነው። በጎ ተግባር ማለት ልብና ነፍስ የረጋበትና የሰከነበት ነገር ነው። ወንጀል ማለት ደግሞ ልብህ ለርሱ ሳይከፈት ነፍስህ ውስጥ የተመላለሰ፣ የከነከነህ አሻሚ ነገር ነው። ስትሰራው ወንጀል ይሆን እያልክ ቀልብህ ውስጥ ጥርጣሬ የሚከሰትበትና የምትፈራው፣ ፀያፍ ስለሆነም አርአያ የሚሆኑ፣ ታላላቅና የተሟላ ስብዕና ያላቸው ሰዎች ፊት ጉዳዩ እንዲታወቅብህ የማትፈልገው ጉዳይህ ነው። ይህም ነፍስ በተፈጥሮዋ ሰዎች መልካም ስራዋን እንዲያውቁላት ነው የምትፈልገው። አንዳንድ ስራዋ ይፋ መውጣቱን ከጠላች ግን ያ ስራ ወንጀል ነውና ምንም መልካም የለውም። በነፍስህ ውስጥ ይህ የብዥታ ምልክት እስካለና በነፍስህ ውስጥ እስከተመላለሰ ድረስ ሰዎች ፈትዋ ቢሰጡህ እንኳ የነርሱን ፈትዋ እንዳትወስድ! ምናልባት ፈትዋ ሰጪው ያለእውቀት ፈትዋ ሰጥቶበት ሊሆን ስለሚችል የጉዳዩ ብዥታነት ትክክለኛ እስከሆነ ድረስ ፈትዋው ብዥታውን የማስወገድ አቅም የለውም። ነገር ግን ፈትዋው የተሰጠው በትክክል የሸሪዓ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ከሆነ ፈትዋ ጠያቂው ልቡ ለመልሱ ክፍት ባይሆንም እንኳ የግዴታ ወደ ፈትዋው ሃሳብ መመለስ ግዴታ ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/66540